

# አልሙለኽሱል ፊቅሂዩ ሚን ዑሉሚል ኢማሚል አልባኒዩ

በአህመድ ሲራጅ ሙሀመድ

ይህ አጭር የpdf ማስታወሻ ሸይኽ ሱለይማን ሙባረኪ ረሒመሁሏህ “አልሙለኸሱል ፊቅሂዩ ሚን ዑሉሚል ኢማሚል አልባኒዩ” በሚል ርእስ ከተለያዩ የሸይኽ አልባኒ የጽሁፍና የድምጽ ፋይሎች በማጠናቀር ካዘጋጁት ኪታብ የአራተኛው ምእራፍ (ስለጾም የሚያትተው) ምእራፍ ትርጉም ነው። ኪታቡ በጣም ወሳኝ ወሳኝ ቁምነገሮችን ያካተተ ስለሆነ ትርጉሙን በማንበብና ለሌሎችም ይደርስ ዘንድ በማሰራጨት የአጅሩ ተካፋይ ይሁኑ።

# ምእራፍ 4፡ ጾም

## ንኡስ ምእራፍ (1)

- የረመዷንን ወር መጾም ግዴታ ነው።

- የጾም ዋነኛ አላማው ጾመኛው አላህን መፍራትንና ወደእሱው መቃረብን እንድጨምርለት ማድረግ ነው። ስለዚህ የጾም በቸኛውና ዋነኛው አላማ ጾመኛው ራሱን ከምግብ፣ መጠጥና ግንኙነት ማቀቡ አይደለም።

## ንኡስ ምእራፍ (2)

- በእያንዳንዷ የረመዷን ሌሊት ለእያንዳንዷ ቀን ጾም ኒያን መነየት ግዴታ ነው።

- ማንኛውም ለአቅመ አዳም የደረሰ፣ ጤናማ አዕምሮ እና የመጾም አቅም ያለው ሙስሊም ሁሉ ረመዷንን የመጾም ግዴታ አለበት ።

- ሱሁር (ሌሊት መመገብ ወይም መጠጣት) ግዴታ ነው።

# ንኡስ ምእራፍ (3)

- የረመዷን ጨረቃ ከተሸፈነች (በደመና፣ በአቧራና በመሰል ነገራቶች) የሸዕባንን ወር አሟልቶ (30 አድርጎ) ማስላት ተገቢ ነው።

- ጾም የሚጾመው ሙስሊሞች በሚጾሙበት ቀን ነው። የሚፈጠረውም (ዒድ የሚከበረውም) ሙስሊሞች በሚያፈጥሩበት እና በሚያከብሩበት ቀን ነው።

- ከረመዷን መግባት እንድሁም ከዒዶች ጋር ተያይዞ የጨረቃ የመውጫ ጊዜ መለያየት ታሳቢ አይደረግም። ይህም ማለት በየትኛውም የዐለም ክፍል ቢሆን የጨረቃ መታየት ከተረጋገጠ በሁሉም ሀገራት ያሉና ጾሙ የሚመለከታቸው ሙስሊሞች በሙሉ የመጾም ግዴታ አለባቸው ማለት ነው።

- የረመዷንን ጨረቃ ብቻውን የተመለከተ ከማህበረሰቡ ጋር ይጹም። ከማህበረሰቡ ጋር ያፍጥር። (ብቻውን ጨረቃን ስለተመለከተ ብቻ ከሰዎች ተለይቶ ብቻውን በጾም ማሳለፍ ወይም ዒድን ማክበር አይፈቀድለትም።)

- ጨረቃዋን ያያት ብቻውን በሚኖርበት ሀገር (ሌሎች ሙስሊሞች በሌሉባት ሀገር) ላይ ሆኖ ከሆነ ግን ብቻውን የመጾም ግዴታ አለበት።

- የጨረቃ ምልከታ በዐይን እይታ እንጅ በስነፈለክ ስሌት መሆን አይችልም።

- የቀኑ ክፍለ ጊዜ በጣም በሚረዝምባቸው ሀገራት የሚኖሩ ሙስሊሞች ጸሃይዋ እስከምትጠልቅ ድረስ መጾም አለባቸው። የቱንም ያክል ቀኑ ቢረዝም በሚኖርባት ሀገር ቀንና ሌሊት እስከተፈራረቁ ድረስ ጸሀይ ሳትጠልቅ ማፍጠር አይፈቀድላቸውም።

- ጸሀይ የምትባልን ነገር የማይመለከቱ ሰዎች (ሁሌም ሌሊትን የሚያሳልፉ ሰዎች) ግን የሌሊትን እና የቀንን የተለመደውን የሰአት ልዩነት በማስላት መጾምና ማፍጠር ይኖርባቸዋል።

# ንኡስ ምእራፍ (4)

- ኢፍጧር የሚፈቀደው ጸሀይ ስትጠልቅ ነው። አዛንን ባይሰማም እንኳ ጸሀይዋ መጥለቋን ያረጋገጠ ጾመኛ ሁሉ ኢፍጧሩን ማፋጠን ይኖርበታል። (ምክንያቱም ኢፍጧር ከጸሀይ መጥለቅ ጋር እንጅ ከመግሪብ አዛን ጋር የተሳሰረ አይደለም።)
- በእርጥብ ተምር (ሩጦብ) ማፍጠር ተወዳጅ ነው። ይህ ካልተገኘ ግን በደረቅ (በበሰለው ተምር) ያፍጥር። ይሄም ካልተገኘ ዉሃን ጎንጨት ይበል።
- አንዳችሁ ሰሁሩን እየጠጣ ባለበት ወቅት የፈጅርን አዛን ከሰማ የሚፈልገውን ያክል ሳይጠጣ እቃውን አያስቀምጥ።
- ከአዛን ቀደም ብሎ ከምግብና ከመጠጥ መቆጠብን (ኢምሳክ) እንደ አምልኮት ወይም ሱንና በመውሰድ መተግበር ቢድዓ ነው።

# ንኡስ ምእራፍ (5)

- የጾም ግዴታነት ቀን ላይ ያጋጠመው (ለምሳሌ የአእምሮ ህመምተኛ በረመዷን ቀን ላይ ቢሻለው፣ ህጻን ለአቅመ አዳም የደረሰው በረመዷን ቀን ላይ ቢሆን፣ ካፊር በረመዷን ቀን ላይ ቢሰልም፣ የረመዷን ጨረቃ መታየቷ የተነገረው ቀን ላይ ቢሆን) እነዚህ ሰዎች ጾሙ ግዴታ የሚሆንባቸው ከዚሁ ሰአት ጀምሮ ነው። በማለዳው ክፍለጊዜ ላይ ቢመገቡም፣ ቢጠጡም፣ ጾምን ከሌሊቱ ባይነይቱም'እንኳ ግዴታ እንደሆነባቸው ባወቁበት ወቅት ላይ የረመዷንን ጾም በመነየት መጾም ነው የሚጠበቅባቸው እንጅ የተወሰነው የጾም ሰአት አልፎናል ወይም በቀኑ ክፍለጊዜ በልተናል በሚል የተሳሳተ ምክንያት የረመዷንን ጾም ሊያሳልፉ አይገባቸውም።

- ህጻናት ጾምን እንድለማመዱ ማድረግ ተገቢ ነው።

- የሱናን ጾም የሚጾም ሁሉ ራሱን አዛዝ ነው። ከፈለገ ጾሙን ይሞላል። ካልፈለገ ደግሞ የጀመረውን ጾም አቋርጦ ያፈጥራል። (ቀዷእ ማውጣት አይጠበቅበትም።)

- ጾመኛ ሆኖ ሳለ ሰዎችን የዘየረና ማፍጠር ያልፈለገ ሰው ለዘየራቸው ሰዎች ዱዓእ ያደርግላቸዋል።

# ንኡስ ምእራፍ (6)

- ሰኞን እና ሀሙስን መጾም ሱንና ነው።
- ዓሹራእንም መጾም እንድሁ ይወደዳል። የዓሹራእ ጾም መጀመሪያ ላይ ግዴታ ነበር። የረመዷን ጾም ግዴታ መሆንን ተከትሎ ነው ግዴታነቱ የተሻረው።
- በዓሹራእ ቀን መደሰት፣ ቤተሰብን ማስደሰት፣ እለቱን ዘና ፈታ እያሉ ማሳለፍ በምንም አይነት ሀዲስ አልተደነገገም።
- ሀጅ ላይ ላልሆነ ሰው የዐረፋን ቀን መጾም ይወደዳል።
- የሙሐረምን ዘጠነኛውን ቀን (ከዓሹራእ በፊት ያለውን ቀን) መጾምም ይወደዳል።
- በየወሩ ጨረቃ ሙሉ የሚሆንባቸውን ሶስት ቀናት እንድሁም የሸዋልን ስድስቱን ቀናት መጾም ሱና ነው።
- ቀደም ያሉትን የሸዕባን ቀናቶች የመጾም ልምድ ላለው ሰው ከሸዕባን አጋማሽ በኋላም መጾም ይፈቀድለታል።
- የረጀብን ወር እንድሁም እለተ ጁሙዓን እና እለተ ቅዳሜን በጾም መለየት ክልክል ነው።

- እለተ ቅዳሜ ተወዳጅ ከሆነ የጾም ቀን ጋር ቢገጥም'እንኳ መጾም አይቻልም። ከጁሙዓ ጋር አጣምሮም ቢሆን ቅዳሜን በጾም ማሳለፍ አይፈቀድም። የግደታ በሆነ ጾም ላይ ግን ቅዳሜን መጾም ግዴታ ነው። ለምሳሌ የረመዷን ጾም ወይም በተከታታይ የሚጾም የማካካሻ ጾም ላይ።

- ሁለቱን የዒድ ቀናት መጾምም ይከለከላል።

- ከዒደል አድሃ ቀጥለው ያሉትን ሶስት ቀናትን (አያመ ተሽሪቅን) መጾምም አይፈቀድም። ዑምራን ከዚያም ሀጅን ለመፈጸም (ተመቱዕ) ነይቶ ግን ደግሞ ሀድይ (የእርድ እንስሳን) ማቅረብ ያልቻለ ሰው ብቻ እነዚህን 3 ቀናት በጾም ማሳለፉ ይፈቀድለታል።

- ሁል ጊዜ መጾም ክልክል ነው።

- ሳያፈጥሩ ተከታታይ ቀናትን መጾምም እንድሁ ይከለከላል። እስከ ሌሊት (ሰሁር እስከመመገቢያ ወቅት ድረስ) ሳያፈጥሩ በጾም መቀጠል ግን ይፈቀዳል።

# ንኡስ ምእራፍ (7)

- የመልካም ስራዎች ምንዳ በረመዷን ላይ ተባዝቶ እንድሚመዘገብ ወይም ተደራርቦ እንደሚታሰብ የሚጠቁም ግልጽ የሆነ መረጃ የለም። ወንጀሎችም ተባዝተው እንደሚመዘገቡ የሚጠቁም አንድም ግልጽ መረጃ የለም። በጥቅሉ መልካም ስራዎችም ይሁኑ ኃጢያቶች በቦታዎች እና በጊዜያት ደረጃ ምክንያት እንደሚገዝፉ ወይም ተባዝተው እንደሚመዘገቡ ጠቋሚ ግልጽና ትክክለኛ የሆነ መረጃ የለም።

# ንኡስ ምእራፍ (8)

- ያለሸሪዐዊ ምክንያት ጾሙን ያቋረጠ (ያፈጠረ) ወይም ከመነሻውም ያልጾመ ሰው ያፈጠረባቸውን ቀናት ቀዷእ አይጾምም። ተውበት የማድረግ ግዴታ ነው ያለበት ።
- ጾመኛ ሰው ዋግምት (ሂጃማ) መጠቀም ይፈቀድለታል።
- ጾመኛ ባል በሚስቱ መሳሙም ይፈቀዳል። ባይሆን ግን በዚህ ጉዳይ ላይ በወጣትና በሽማግሌ መካከል የብይን ልዩነት አለ።
- ጾመኛ ባል ሚስቱን መነካካትና መደባበስ ይፈቀድለታል። ብልቷ ውስጥ ሳያስገባ እስከሆነ ድረስ በመቀራረባቸው ወይም በመነካካታቸው ምክንያት የዘር ፈሳሽ (ስፐርም) ቢፈሰው ጾሙ አይበላሽበትም።
- ራስን በራስ ማርካት ክልክል ነው። ሆኖም ግን ጾምን አያበላሽም።
- ለጾመኛ ሰው ጥርስን መፋቅ ይፈቀድለታል።
- ኩል መኳል እና አክታን መዋጥም ጾምን አያበላሹም።
- የደረት ህመም ያለባቸው ሰዎች (አስምና መሰል በሽታዎች) በአፍ ላይ የሚነፉ ስፐሬዮችን መጠቀም ይፈቀድላቸዋል።

የመድሀኒቱን ጣዕም እስካላገኙ ድረስ ጾማቸውን አያበላሽባቸውም።

- ሲጋራ ማጨስና፣ በአፍንጫ የሚሳቡ መድሃኒቶችን፣ ትንባሆንም ጭምር በአፍንጫ መጠቀም ጾምን ያበላሻሉ።
- የህክምና መርፌዎች በሁለት ይከፈላሉ። የምግብነት ይዘት ያላቸው ከሆኑ ጾምን ያበላሻሉ። ምግብ ነክ ይዘት የሌላቸው ከሆኑ ደግሞ ጾምን አያበላሹም።
- የሚያስፈጥርን ነገር እስካልያዘ ድረስ ለህክምና ምርመራ አላማ በጉሮሮ የሚገባን ቱቦ (ኢንዶስኮፒ) መጠቀም ይቻላል።
- የማደንዘዣ መርፌ እንድሁም የዐይን እና የጆሮ ጠብታዎች ለጾመኛ የተፈቀዱ ናቸው።
- ሆን ብሎ በራስ ምርጫ እስካልሆነ ድረስ ትውከት ጾምን አያስፈታም።
- ጾምን በማሟላት ላይ ግራ መጋባት (ልጠናከርና ልጨርስ ወይስ ላቋርጠውና ላፍጥር በሚል ከራስ ጋር ማውራት) ጾምን አያበላሽም።
- ዉዱእ በሚያደርጉበት ወቅት በስህተት ዉሃን መዋጥ ጾምን አያበላሽም።

# ንኡስ ምእራፍ (9)

- ወሲባዊ ግንኙነት ጾምን ያፈርሳል። ማካካሻም ያስፈልገዋል። ማካካሻውም በቅደም ተከተል ነው የሚሆነው። የግንኙነቱ ምክንያት ሴቷ ብትሆንም'እንኳ ማካካሻው የሚመለከተው ግን ወንዱን ብቻ ነው።

- በአንዱ የጾም ቀን ላይ ደጋግሞ ግንኙነት የፈጸመ ጾመኛ አንድ ማካካሻ ነው የሚጠበቅበት። ግንኙነቱ በተለያዩ ቀናት ከተፈጸመ ግን ለእያንዳንዱ ግንኙነት ለፈጸመበት ቀን ራሱን የቻለ ሙሉ ማካካሻ ያስፈልገዋል።

- የትኛውንም አይነት ማካካሻ ቢፈጽም ጾም ያፈረሰባቸውን ቀናት የመጾምም ግዴታ እንዳለበት መዘንጋት የለበትም።

- ካሳው ግዴታ የሚሆንበት በግንኙነቱ ከመርካት ጋር ብቻ ተያይዞ ሳይሆን የዘር ፈሳሽ ወጣውም አልወጣውም ሁለቱ የተገረዙ የሰውነት ክፍሎች ከመነካካታቸው ጋር ተያይዞ ነው።

**ማካካሻውም፡**

- ባርያን ነጻ ማድረግ፣ ይህን ያልቻለ በተከታታይ 2 ወራትን መጾም፣ ይህን ያልቻለ ደግሞ 60 ደሃዎችን መመገብ ነው።

- በረመዳን ቀን ከትዳር አጋሩ ጋር ጉዞ የወጣና ግንኙነት የፈጸመ ጾመኛ ምንም ችግር የለበትም። ምንም አይነት ማካካሻ ቅጣት አይመለከተውም። ምክንያቱም ለተጓዞች የተፈቀደን ተግባር ነው የፈጸመው። (ሙሳፊር በሚያስብል ጉዞ ላይ ያለ ሰው ከመነሻውም አለመጾም ይፈቀድለታል። ከጾመም በመሃል ማፍረስ ይችላል።)

# ንኡስ ምእራፍ (10)

- የግዴታንም ይሁን የሱናን ጾም በመጾም ላይ ያለና ረስቶ ወይም ተሳስቶ የተመገበ እሱ ጾመኛ ነው። ስለዚህ ጾሙ ትክክል ነውና በጾሙ ይቀጥል። ቀዷእ ማውጣት አይጠበቅበትም።
- ቀዷእ የሚጾም ሰው በተከታታይም ይሁን አለያይቶ (በመሀል በመሀል እያፈጠረ) መጾም ይፈቀድለታል።
- ቀዷእን ለማውጣት ምቹ አጋጣሚ ያገኘ ሁሉ ተጣድፎ ቀዷውን የማውጣት ግዴታ አለበት ።
- ቀጣዩ ረመዷን እስከሚደርስበት ድረስ ከባለፈው ረመዳን ጾም ላይ ያለበትን ቀዷ ያላወጣ ሰው መጾም በሚችልበት ወቅት ቀዷውን ከማውጣት ዉጭ ሌላ ማካካሻ አይጠበቅበትም።
- የረመዷን ቀዷእ ያለባት ሴት የሸዋልን 6 ቀናት ከመጾሟ በፊት ቀድማ ቀዷዋን ማውጣት አለባት ።
- ስድስቱን የሸዋል ቀናት ለመጾም 6ቱንም ቀናት ማከታተል እንደ ቅድመሁኔታ ተደርጎ አይወሰድም። በመሀል እያፈጠሩ መጾም ይቻላል።

- በህመም ምክንያት ያፈጠረ ሰው ጤናው ሲስተካከልለትና መጾም ሲችል ያልጾማቸውን ቀናት ቀዷእ ማውጣት አለበት።

- ያጋጠመው ህመም የማይሻለው አይነት መሆኑን የህክምና ባለሙያዎች ካሳወቁት ግን በእያንዳንዱ የረመዷን ቀን አንድን ምግብ ለአንድ ሚስኪን ይመግባል።

- አጥቢና እርጉዝ ሴት መጾሟ እራሷን ወይም ህጻኑን ወይም ጽንሱን ይጎዳብኛል ብላ ከሰጋችና በዚህም ምክንያት ካፈጠረች ቀዷእ ማውጣት ሳይሆን በእያንዳንዱ ባፈጠረችባቸው ቀናት ልክ ለአንድ ሚስኪን አንድን ምግብ መመገብ ነው የሚጠበቅባት ።

- ሀይድ ላይ ያለች ሴት አትጾምም። ቀዷእ ግን ታወጣለች ።

- የበሽታ ደም ያጋጠማት ሴት መጾም አለባት። አለመጾም አይፈቀድላትም።

- ጾም ለመጾም ስለትን (ነዝር) ፈጽሞ ነገር ግን ስለቱን ሳይሞላ ለሞተ ሰው ቤተሰብ ይጾምለታል።

- የረመዷንን ጾም ግን ማንም ሰው ለማንም ሰው መጾም በፍጹም አይፈቀድለትም። (ለሞተ ሰውም ቢሆን።)

- መንገደኛ ሰው ከፈለገ መጾም ካልፈለገ ደግሞ ማፍጠር ይችላል።

- **ጉዞ ላይ ያለ ሰው ጾሙ የሚጎዳው ከሆነ መጾሙ ክልክል ይሆንበታል።**
- **ማፍጠር የሚቻልበት ጉዞ በአካባቢው ባህልና ልማድ መሰረት መንገደኛ የሚያስብል ጉዞ ነው።**
- **ጉዞ ለመውጣት የወሰነ ሰው ከቤቱ ሳይወጣና ጉዞ ሳይጀምር ቀድሞ ማፍጠር ይችላል።**

# ንኡስ ምእራፍ (11)

- ኢዕቲካፍን በረመዷንም ይሁን ከረመዷን ዉጭ ባሉት የአመቱ ቀናት ላይ መፈጸም ሱና ነው። በረመዷን ደግሞ የበለጠ የጸና ሱንና ይሆናል።
- ኢዕቲካፍ በሶስቱ መስጅዶች ብቻ ነው የተፈቀደው። (በመስጂደል ሀረም፣ በመስጂደ ነበዊይ እና በመስጂደል አቅሷ ብቻ።)
- ኢዕቲካፍ የሚያደርግ ሰው ጾመኛ መሆኑ ግዴታ ነው።
- ኢዕቲካፍ ላይ ያለ ሰው የሚያስፈልጉትን ጉዳዮች ለመከወን ከኢዕቲካፍ በታው መውጣት ይፈቀድለታል።
- ሆኖም ግን ሙዕተኪፍ ህመምተኛን አይጠይቅም። ሚስቱን አይነካም፣ አይደባብስም።
- ሙዕተኪፍ ከመስጂዱ መጨረሻ አካባቢ (ከመስጂዱ መግቢያ በር አቅራቢያ ላይ) ትንሽን ድንኳን ነገር ማስቀመጥና በዚያች ክፍል ውስጥ ሆኖ ማሳለፍ ይችላል።

- ሚስት ኢዕቲካፍ ላይ ያለን ባለቤቷን መዘየር ይፈቀድላታል። እሱም ልትዘይረው የመጣችዋን ሚስቱን እስከመስጂዱ በር ድረስ መሸኘት ይችላል።
- ሚስት ከባሏ ጋር አብራው ኢዕቲካፍ ማድረግም ትችላለች።
- ኢዕቲካፍ በወሲብ ግንኙነት ሙሉ በሙሉ ይፈርሳል።
- ከረመዷን ሌሊቶች ሁሉ በላጯ ሌሊት ለይለተል ቀድር ነች።
- በተሻለው የመረጃ ድጋፍ መሰረት ለይለተል ቀድር በ27ኛዋ የረመዷን ሌሊት ነው የምትገኘው። (ከዚች ሌሊት ዉጭ ወዳሉት ሌሊቶች አትዘዋወርም።)

<u>**አልሙለኸሱል ፊቅሂዩ ሚን ዑሉሚል ኢማሚል አልባኒዪ**</u>

**ከተሰኘው ኪታብ ውስጥ ስለ ጾም የሚያትተው ምእራፍ (ኪታቡ አ'ሲያም) ትርጉም በዚህ ተጠናቀቀ።**